## ከከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የተሰጠ ማስታወቂያ

### ሴንትራል የጤና ኮሌጅን በተመለከተ

ሴንትራል የጤና ኮሌጅ በአዲስ አበባ ቦሌ እና ላንቻ፣ በባህርዳር፣ በሀዋሳ እና በአዳማ ካምፓሶች በዲግሪ መርሃግብር የእውቅና ፈቃድ ተሰጥቶት በማስተማር ላይ እንደነበረ ይታወቃል። ይሁንና ተቋሙ ለትምህርት ሚኒስቴር በ13/02/2007 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ በኪሳራ ምክንያት በዲግሪ መርሃግብር ትምህርት መስጠት መቀጠል አለመቻሉን አሳውቋል።

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 81 /1/ሐ መሰረት ተቋሙ ሲፈርስ ወይም ስራውን ሲያቆም የእውቅና ፈቃዱ እንደሚሰረዝ በግልጽ ተደንግጓል። የእውቅና ፈቃዱ የተሰረዘ የግል ተቋምም ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን አግባብነት ባላቸው ሌሎች ተቋማት እንዲፈጽሙ ማድረግ እንደሚኖርበት የተደነገገ ቢሆንም ተቋሙ ግን ይህን ተግባራዊ አላደረገም።

ስለዚህ ሴንትራል የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከላይ ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ በማስተማር ተግባር ላይ ተሰማርቶ የማይገኝ ተቋም መሆኑን እናስታውቃለን።

የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ

## ከከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የተሰጠ ማስታወቂያ

ሴንትራል የጤና ኮሌጅ በአዲስ አበባ ቦሌ እና ላንቻ፣ በባህርዳር፣ በሀዋሳ እና በአዳማ ካምፓሶች በዲግሪ መርሃግብር የእውቅና ፈቃድ ተሰጥቶት በማስተማር ላይ እንደነበረ ይታወቃል።

ይሁንና ተቋሙ ለትምህርት ሚኒስቴር በ13/02/2007 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ በኪሳራ ምክንያት በዲግሪ መርሃግብር ትምህርት መስጠት መቀጠል አለመቻሉን አሳውቋል። በመሆኑም ቀደም ሲል ሴንትራል የጤና ኮሌጅ ስልጠና ሲሰጥባቸው በነበሩ ካምፓሶች

የሚሰጥ ማናቸውም ትምህርትና ስልጠና እውቅና የሌለው መሆኑን እንገልጻለን። ከዚህም ባሻገር ከዚህ በኋላ በተቋሙ ስም የሚመጡ የትምህርት ማስረጃዎች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን እያስታወቅን፣

በተጨማሪም በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 81 /1/ሐ መሰረት ተቋሙ ሲፈርስ ወይም ስራውን ሲያቆም የእውቅና ፈቃዱ እንደሚሰረዝ በግልጽ የተደነገገ ሆኖ እያለ ቀደም ሲል የሴንትራል የጤና ኮሌጅ በነበሩ ካምፓሶች ላይ ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ ስሙን በመለጠፍ የሚሰጠው ስልጠናም ሆነ የአዲስ ተማሪ ምዝገባ ሕጋዊ አለመሆኑን እንገልጻለን።

የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ